**Ethiopian National Transitional Council**
P.O.Box 9929
Alexandria, VA 22304
Tel: 1-703-659-6000 (US and Canada)
Tel: +44-7958-487-420 (Europe and Africa)
Email: contact@etntc.org
Website: www.etntc.org

April 1, 2014

# የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሽግግር ምክር ቤት በሀገራችን ኢትዮጵያ ላለው ሁለንተናዊ ቀውስ ግልፅ የሆነ የአማራጭ መፍትሄ አለው።

በሀገራችን ያለው የዕለት ከዕለት የሰብዓዊ መብት ረገጣ፣ በዘር ከፋፍሎ ማጋጨትና፣ ሥር የሰደደው የወያኔ ሙስና በብዙ ሕዝብ ዘንድ አሜን ብሎ መቀበል የተለመደ ሆኗል። ሌሎች የሕብረተሰቡ ክፍሎች ደግሞ ተስፋ በመቁረጥ ግፉን ተቀብለው ይኖራሉ። **የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሽግግር ምክር ቤት ተስፋ መቁረጥ አማራጭ ነው ብሎ አያምንም።**

በቅርቡ የአማራ ተወላጅ የሆኑ ገበሬዎችን እንደተለመደው በዘር መርጦ በማሳደድ ከምዕራብ ኢትዮጵያ ማፈናቀል፤ የሙስሊም እምነት ተከታዮች የወያኔን በሀይማኖት ጣልቃ ገብነት በመቃወም የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በጭካኔ ማፈን፤ የአሬና ትግራይ ፓርቲ አባላትን በትግራይ ማሰር፤ በርካታ የኦሮሞ ወጣቶችንና ወገኖችን እንዲሁም በአርባ ምንጭ ከተማና አካባቢ የሚኖሩ ሰላማዊ ዜጎችን በጅምላ ማሰር፤ ለረጅም ጊዜ የሀይማኖት መሪዎችን፣ ጋዜጠኞችንና የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችን በእስር ማቆየት፤ እነኝህ ድርጊቶች ሊቆሙ የሚችሉት ነፃነትን የሚሹ ኢትዮጵያውያን ትብብር በመፍጠር ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከእዚህ ዘረኛ የአፓርታይድ አገዛዝ የተሻለ አማራጭ ሲያቀርቡ ነው።

የህወሀት ሥርአትን በማስወገድ ሁሉን አቀፍ የሆነ ህዝባዊ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ሀገራችንን ጠፍንጐ ከያዛት የፖለቲካ፤ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውስ ነፃ የሚያወጣ ግልፅ መፍትሄ ነው።

በቅርቡ በአንድነትና በሰማያዊ ፓርቲ እየተደረገ ያለው ሀገር አቀፍ የሆነ ኢትዮጵያውያንን የማስተባበርና የመታገል እንቅስቃሴ ኢትዮጵያውያን ለነፃነታቸው ለሚደርጉት ትግል አዎንታዊ እርምጃ ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሽግግር ምክር ቤት ይህንን ታላቅ ጥረት ሙሉ በሙሉ ይደግፋል። በተጨማሪም የሽግግር ምክር ቤቱ ድምፃችን ይሰማ በሚያደርገው እንቅስቃሴና የኢትዮጵያ ሙስሊም ሀይማኖት ተከታይ ወገኖቻችን፤ የህወሀት አገዛዝ የሚያደርገውን የሀይማኖት ጣልቃ ገብነትን ለማስቆም የሚያካሂዱትን ቁርጠኝነት የተሞላበት የሰላማዊ እንቅስቃሴ ያደንቃል።

የእነኚህ ጥረቶች ቀጣይ የአመክንዮ እርምጃ ሁሉም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ተባብረው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተሻለ ተተኪ የአማራጭ መፍትሄ ማቅረብ ነው። ይህንን ሂደት ለማስተባበርና ለማመቻቸት የሽግግር ምክር ቤቱ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥ የሆኑ የምክክር ስብሰባዎችን ላለፉት ሁለት ዓመታት በተለያዩ ከተማዎች አካሂዷል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሽግግር ምክር ቤት በሚቀጥለው ሚያዝያ 5 ቀን 2006 (April 13, 2014) ወቅታዊና በጣም አስፈላጊ ህዝባዊ ስብሰባ በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ ያካሂዳል። በእዚህም ስብሰባ ላይ የሃይማኖት መሪዎች፣ ታዋቂ ምሁራን፣ የፖለቲካና የሲቪክ ማሕበራት መሪዎች በተባበረ ትግል የህዋት ስርአትን በማስወገድና በመተካት፤ እንዲሁም በኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ ህዝባዊ የሽግግር መንግስት ምስረታን መሰረት በመጣል ሂደት ላይ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎና ሚና ምን መምሰል እንዳለበት ማብራሪያና ትንታኔ ይሰጣሉ።

የዕለቱ ተናጋሪዎች አቡነ ፊሊፖስ፣ ሼክ ኻሊድ መሀመድ፣ ኡስታዝ ሀጂ ነጂብ፣ አባ ገብረሥላሴ ጥበቡ፣ ፐ/ር አለማየሁ ገብረማርያም፣ ዶ/ር ካሣ ከበደ፣ ጋዜጠኛ አበበ ገላውና የሽግግር ምክር ቤቱ አፈ ጉባዔ አቶ ስለሺ ጥላሁን ይሆናሉ።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሽግግር ምክር ቤት በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ አካባቢ ለሚገኙ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በዚህ ህዝባዊ ስብሰባ ላይ እንዲገኙ በትሕትና ይጋብዛል።

ቀንና ሰዓት፡ እሁድ ሚያዝያ 5 ቀን 2006 (ሰባት ተኩል)
Time/Date: Sunday, April 13, 2014, at 1:30 PM

ቦታው፡ ሸራተን ፔንታገን ሲቲ (ዳማ ምግብ ቤት አጠገብ)
Place: Sheraton Pentagon City, 900 S. Orme Street, Arlington VA (Next to Dama Restaurant)

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሽግግር ምክር ቤት አመራር